# <u>በስማችንና በተግባራችን እንጠራ ዘንድ</u>

ከአቦ አራዳ አባ ሻውል

ጥቅምት ፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም
*October 13, 2014*

ከታጋይ የሃይማኖት አባቶች፣ ጳውሎስና ጴጥሮስ፤ ከፖለቲካ መድረክ ነፃነትና አርነት የሚባሉ ሥሞችና ፅንሰ-ሓሳቦች በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ ጎልተው ሕዝብን ለስደት፤ ለእስርና ለሞት አድርሰዋቸዋል። ለምን ቢባል "አብዮት" አሊያም ሪቮልሽን የሚባለው ፅንሰ-ሐሳብ - Concept እና ንድፈ-ሐሳብ - Theory- የሚባሉ ከተግባር (application) ባለመዛመዳቸው መላ ቅጡ እየጠፋ ስለሄደ ነው። እሱ ብቻ አይደለም መገናኛውም ነጥባዊ (ዲጂታል) ስለሆነ ነው።

በተለይም በኢትዮጵያና በኤርትራ የተካሄደው "አብዮት" የሚል ቃል ውስብስብ አድርጎታል። በጦርነትና በአብዮት መኻል ያለ ልዩነት ማሳየትና ማስረዳት አልተቻለም። በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም የተመራው የደርግ መንግሥት አብዮታዊ እንዳልነበረ ግልጽ ሆነ። በመለሰ ዜናዊ የተመራው መንግሥት አብዮታዊ እንዳልነበረ አሁንም በገሀድ ወጣ፤ በኢሳያስ አፈወርቅ የሚመራው መንግሥት አብዮታዊ እንዳልነበረና እንዳልሆነ ለብዙኃኑ ግልጽ እየሆነ መጥተዋል። ይህንን ዕውነታ የሚክድ ካለ በጭንቀት ውስጥ የተዘፈቀ አሊያም በቅጀት ሰመመን የሚኖር መሆን አለበት።

ታድያ በኢትዮጵያና በኤርትራ የተካሄደው አብዮት ምን ዋጠው? የተፈለገው ትክክለኛው አብዮት ምን ነበር ማነውስ የሚመራው? ስለሁኔታው ለማስረዳት ያህል አብዮት በኢትዮጵያ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት እንደሚከተለው ይገለጣል። ሦስት ጣምራ ጠላቶች ነበሩ  የሰው ሳይሆን የሥርዓት ጠላት እነሱም፡-

1. ባላባታዊ - Feudalism
2. ቢሮክራሲያዊ - Bureaucratic Capitalism እና
3. ኢምፐሪያሊዝም - Imperialism ነበሩ/ናቸውም

ከላይ የተጠቀሱ ፅንሰ-ሐሳብና ንድፈ-ሐሳቦች ለመተግበር ከፍተኛ ትንንቅ ተካሂዷል፤ እየተካሄደም ይገኛል። ዝርዝሩ በዚህ ጽሁፍ የሚገለጥ አይደለም።

ታዲያ ለመተግበር ያስቸገረው ለምንና እንዴት ነበር? ትክክለኛ ጥያቄ ነው። መልሱ ግን ከበድ ይላል። ፅንሰ-ሐሳብ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ማመን ግዴታ ነው አለበለዚያ መግባባት ፈጹሞ አይቻልም። ሠፊው ሕዝብ የሚገባው ፅንሰ-ሐሳብ በተግባር ሲተሮገም ብቻ ነው። ንድፈ-ሐሳብ የሚመለከተው ምሑራንን ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት በሠፊው ሕዝብና በተራው ሕዝብ ትልቅ ልዩነት ስለአለና ስለነበረ ጉዳዩ ቀላል አይሆንም። ዴሞክራሲያ የሚለው ፅንሰ-ሐሳብ እና አመራር የሚለው ቲዮሪ ማቀነባበር በጣም ከባድ ሆኖ ይመስለኛል። የኢሕአፓ ትልቁና ዋናው ድክመቱ እነዚህን ሁለት መንታዎች በተራ ቃንቃ ባለማስረዳቱ ይመስለኛል። በተግባር ግና ዴሞክራሲያዊና የጋራ አመራርን ይተገብራል። በሕቡዕ ስለሆነ ግና ለሰፊው ሕዝብ አይታይም።

ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ጣምራ ጠላቶች እንዴት ተገለጠ? እንደሚከተለው ነበር።

ባላባታዊ ማለት ለተራው ሕዝብ በሞፈክር ደረጃ "መሬት ለአራሹ" ተብሎ ሲነገራቸው ገብቶአቸው በትግሉ ተሳተፉ።

ቢሮክራሲ ተብሎ ሲነገር ግና ለብዙኃኑ ከባድ ነበር አሁንም ድረስ ከባድ ነው። የኤርትራ ግንባሮች ቢሮክራሲውን የኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ ብሎው ስለፈረጁ ጉዳዩ ውስብስብ አደረገው። የወያኔ ድርጅት ደግሞ "ቢሮክራሲዊን" ለማስረዳት የአማራን ሕዝብ በጠላትነት ስለፈረጁ በእነሱ ላይ እስኪደርስ ድረስ አልገባቸውም ነበር። እነሱ የሚያውቁት መሪ ካርል ማክስ Karl Marx እንጂ ማክስ ዌበርን Max Weber አያወቁምና ነው። ተራማጅ ቢሮክራሲ እንደነበረና ለወደፊቱም እንደሚኖር አልተገነዘቡም።

በሦስተኛው ደረጃ ግና ለሁላችንም ለማስተማርም ሆነ ለመማር ከባድ ሆኖ የነበረውና ያለው ስለ ኢምፐሪያሊዝም ሲነገር ነው። እንኳን ለእኛ ኢትዮጵያውያንና ለኤርትራውያን ለራሳቸው ለሩሳውያን፣ ለአሜሪካውያንና ቻይናውያንም ጭምር ከባድ እየሆነ መጥተዋል። ለነገሩ መንግሥቱ ኃ.ማርያም ኢምፐሪያሊዝም "ሰው በላው" ሲል የሜኤሶን ድርጅት ደግሞ ኢምፐሪያሊዝምን "የተነፈሰ ጎማ" ብሎ ሲያስተጋባ ኢሕአፓ በበኩሉ "የወረቀት ነብር" ብሎ ነበር።

ታዲያ "የኢትዮጵያ አብዮት" ሦስቱን ጣምራ ጠላቶች በአንድ ላይ ለመጣል አብዮተኞችም ሆኑ ግንባሮች በየበኩላቸው ተዋድቀዋል። ምኑ ላይ ነው የተሳሳቱት? አገባብ ላይ ነው ወይስ አስተሳሰብ? ታሪክ ለማወቅ ለሚፈልግ እየተጣፈና እየተነገረ ነው። ከታሪክ ለመማር ተምሮም መፍትሔ ለመፈለግ ጊዜው አሁን ነው። ለማተራመስም ሆነ ጥቅም ለማግኘት ለምትሯሯጡ ለእንናተም ጊዜው አሁን ነው። ትግል በየፈርጁ ማለት እንዲህ ነው፤ እነሆ እንከራከርና እንቸናነፍ ወይም እንሸናነፍ።

በምሳሌ ለማስረዳት አቡነ ጴጥሮስ የኢጣልያን ቅኚ ግዛት ላለመቀበል በመድፍ ተደብድበዋል። ታጋይ አርበኛ ነበሩ። ልጅ ጳውሎስ (ጓድ ታዬ ጉልላት) የቅኝ ግዛት ቲዮሪ ያነገበውን የሻዕቢያ ድርጅት በመቃወሙ አርበኛ ልንለው እንችላለን። ፋሽሽት ደርግንና ዘረኛው ወያኔን በመታገሉ ደግሞ ጀግንነቱን በሚገባ አረጋግጦልን በቅርቡ ሕይወቱን አጥቷል።

እንዴት ነው ኢሕአፓ አብዮታዊ ድርጅት ሆኖ የቆየውና አሁንም የሚታገለው? የብዙ ሰዎች ጥያቄ ነው። መልሱ ግና ቀላል ነው። የኢሕአፓና የኢሕአፓዎች አሠራርና ዕምነት ከሁሉም ለየት ያለና የነበረ ስለሆነ ነው። ይኸውም ማለት የኢሕአፓ መርሆና እምነት በነፃነትና በአርነት ያለ ጽንሰ-ሐሳብና ንድፈ-ሐሳብ ሲሆን የኢሕአፓዎች ተግባርና ድርጊት ዴሞክራሲያዊ አተገባበርና አሠራር መሆኑን ነው ልዩ የሚያደርገው። ጳውሎስ ጊዚየውን በትምህርት ቤት ብቻ ቢያሳልፈው ኖሮ መአርጉ ዶክተር በሆነ ነበር እሱ ግን ቴዎሪውን በተግባር ያዋለ ከኢሕአፓዎች አንዱ ነበር። ዕምነቱ ደግሞ በድርጅቱ በኢሕአፓ የጠና ነው። ሥሙ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ሕያው ሲሆን ማዕረጉ እንደ ጓዶች ጓድ ነው አለበለዚያ አቶ ይባል። በአንዳንድ ድኅረ ገጾች ዶክተር እያሉ ሲጥፍና ሲለጥፉ ታዝቤአለሁ። ያልሆነውን ማዕረግና ሥም መለጠፍ አግባብ አይደለም ራስን

ማታለል ብቻ ነው። ጳውሎስ የታጋይ መጠሪያው ሲሆን የግሉና የቤተሰቡ መጠሪያ ሥሙ ዘሪሁንና ታዬ ነበር። ዕውነትም ሥሞቹ እሱነቱን የሚገልጡ ናቸው፤ ዘርም ትቶ አልፈዋል በሁሉም ቦታና ሥፍራ ቻይናንም ሳይቀር ታይተዋል።

በነገራችን ላይ በኢሕአፓ ቋንቋ በቅደም ተከተል ማዕርግ እንደሚከተለው ነበር/ነውም።

- አርበኞች - ስለ አገር ብለው የተሰዉ
- ጀግኖች - ስለ ትክክለኛው አብዮት ብለው የተሰዉ
- ሻምፒዮኖች - ስለ መጪው ትውልድ የሚቆረቆሩ

ጓድ ጳውሎስ ሦስቱንም ማዕርግ ተላብሰዋል። ኮከቡን ስለማላውቀው ሌላ የምለው የለኝም። እግዚአብሔር ራሱ ይቀበለው። አሜን።

ጥያቄ ወይም አስተያየት ካላችሁ
በ oboaradashawl@gmail.com